አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) በጤና መስክ ያከናወናቸው ተግባራት

1. የጤና ተቋማት ግንባታ

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) የጤና ኬላዎችን እየገነባ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ማዋል የጀመረው በ1987 ዓ.ም. ነበር። በዚህ ዘመን የተገነቡት የጤና ኬላዎች ብዛት 3 ብቻ ሲሆን፤ ዛሬ በአልማ የተገነቡት የጤና ተቋሞች ብዛት 82 ደራሷል። ከዚህ ውስጥም 76 የጤና ኬላዎች(Health Center)፤ 3 ታዳጊ ጤና ጣቢያና (Cluster Health Center) 3 የእንስሳት ክሊኒክ (Animal Vet. Clinic) ናቸው።

በአልማ የተገነባ የእንስሳት ጤና ኬላ (ሰሜን ወሎ፤ ጉባላፈሮት ወረዳ)

2. የህክምና መሣሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ማሟላት

- የሆስፒታል ቁሳቁስ ዕርዳታ (Medical equipments supply for hospitals) ብዛት 8
- የሽንት ቤት ግንባታ በባሕር ዳር ከተማ (Dry pit latrine in Bahir Dar Town) ብዛት 20
- የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት (Clean water supply for villages) ብዛት 7

ከአልማ ለጎንደር ሆስፒታል የተለገሰ ሆድ ሳይከፍት የኩላሊት ጠጠር ማውጫ መሣሪያ

3. የተዋልዶ ጤና አገልግሎት

አልማ ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ በክልላችን በሚገኙ በ10 ዞኖች 2,904 ወኪሎችን በማሠማራት ከ9 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለሚሆን የህብረተሰብ ክፍል በጤናው ዘርፍ አገልግሎት በመሥጠት ላይ ይገኛል።

ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮም ይህንኑ አጠናክሮ በመቀጠል በክልላችን በሚገኙ 102 ወረዳዎች ውስጥ:-

ከአልማ ለባሕርዳር ሆስፒታል የተበረከቱ የህክምና መሣሪያዎች

- በቤተሰብ ምጣኔ (Family Planning)
- በእናቶችና ህፃናት ጤና እንክብካቤ (MCH)
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር በተለይም የፈቃደኛነት የደም ምርመራ(VCT)፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ በእርግዝና ጊዜ ከእናት ወደ ልጅ እናዳይተላለፍ ማድረግ(PMTCT) እና የዕድሜ ማራዘሚያ መድኃኒት እንዲያገኙ ማድረግ(ART)
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከላከል እና
- በወጣቶች ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ህብረተሰቡን በማስተማር የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል።

አልማ ከገነባቸው የገጠር የንፁህ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች አንዱ

መፀዳጃ ቤት (ባህር ዳር)

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

- በ9 ዓመታት ውስጥ 1,074,310 የሚሆኑ አዲስ ደንበኞችን አፍርቷል፡፡
- 2,437,151 የሚሆኑ ነባር ደንበኖች አሉት፡፡

የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ አርሶ አደር ሴቶች ጋር

የእናቶችና ህፃናት ጤንነት ክብካቤ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፤ ደንበኞችን በጤና ተቋም ደረጃ ወደሚሰጥ አገልግሎት መላክ አንዱ የተዋልዶ ጤና ወኪሎች ተግባር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ደንበኞች ወደ ጤና ተቋም ከሚላኩባቸው አገልግሎቶች መካከል፡-

ሀ- የእናቶች ሪፈራል

እናቶች እንደ ለቅድመ ወሊድ፤ ለወሊድ፤ ለድህረ ወሊድ፤ ለቤተሰብ ዕቅድ፤ ለፊስቱላ ህክምና፤ ለክትባት፤ ለወሊድ መቆጣጠሪያ ተጓዳኝ ጠንቅ (Side effect) እና ለመሣሠሉት የተለያዩ አገልግሎቶች ይላካሉ፡፡ በ9 ዓመታት ውስጥም 656,878 እናቶችን ወደ ጤና ተቋማት ለመላክ ተችሏል፡፡

ለ- የህፃናት ሪፈራል

የተዋልዶ ጤና ወኪሎች ህፃናትን ለተቅማጥ ህክምና፤ ለምግብ ዕጥረት መፍትሄ፤ ለክትባት እና ለመሣሠሉት አገልግሎቶች ይልካሉ፡፡ በ9 ዓመታት ውስጥ 1,487,892 ህፃናትን ወደ ጤና ተቋማት ለመላክ ተችሏል፡፡

ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ

በወኪሎች ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ አንዱ ነው:: ይህም በፈቃደኝነት ላይ ለተመሰረተ የደም ምርመራ፤ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለሚሰጥ ህክምና መላክን ያካትታል:: በ9 ዓመታት ውስጥ የተከናወኑት ተግባራትም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

የተሰጠ አገልግሎት	ክንውን
በፈቃደኝነት ላይ ለተመሰረተ የደም ምርመራ አገልግሎት	147,373
የኤድስ ህክምና	3,160
ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚሰጥ ህክምና	13,902

የወጣቶች ተዋልዶ ጤና

ወጣቱ ራሱን ከኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎች አባለዘር በሽታዎች እንዲከላከል እንዲሁም አምራችና ጤናማ ወጣት ለመፍጠር ማህበሩ ከተለያዩ ረጅ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እያካሄደ ይገኛል::

ተ.ቁ.	ተግባራት	መለኪያ	ክንውን
1	ለወጣቶች ትምህርትና መረጃ ማዳረስ		
	ክ/ጊዜ	በጊዜ	1,410
	አቻ ለአቻ ት/ት መስጠት	በቁጥር	11,920
	ክ/ጊዜ	በጊዜ	775
	አዝናንቶ ማስተማር	በቁጥር	242,180
	ወጣት ለወጣት ውይይት	በቁጥር	39,310
	ክ/ጊዜ	በጊዜ	1,350
	ቡና ጠጡ ኘሮግራም	በቁጥር	38,810
	የተሠራጨ የት/ት መርጃዎች	በቁጥር	94,000
2	ስልጠና መስጠት		
	ለክበብ አመራር	በቁጥር	725
	የአቻ ለአቻ ስልጠና የአመቻች ስልጠና መስጠት	በቁጥር	1,685
3	በሪፈራልና ካውንስሊንግ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች		
	የአቻ ለአቻ ምክር ለቤተሰብ	በቁጥር	7,120
	በፈቃደኛነት የተመሠረተ ምርመራ	በቁጥር	11,540
	የኮንደም ስርጭት	በቁጥር	404,750

- 56 ክበባት ከትምህርት ቤት ውጭ እና 40 በትምህርት ቤት ውስጥ ክበባት ተቋቁመው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡

ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከልና መቆጣጠር

ፊስቱላን መከላከል

በ1999 ዓ.ም. በምስራቅና በምዕራብ ጐጃም እንዲሁም በአዊ ዞኖች በአጠቃላይ በ9 ወረዳዎች በፊስቱላ እንዋጋ ኘሮጀክት አልማ ለህብረተሰቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማዎች:-

- በፊስቱላ የተጎዱ ሴቶችን ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግና ፊስቱላ እንዳይከሰት የመከላከል ሥራ መሥራት
- የክበባትን አቅም በመገንባት ስለ ፊስቱላና ሌሎች የተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ትምህርት በመስጠት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ማከናወን ሲሆኑ፤

የማስፈፀሚያመንገዶቹም:-

- ስለ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ፊስቱላ ማስተማር
- አቻ ላቻ ውይይት
- ቡና ጠጡ ኘሮግራም
- አዝናንቶ ማስተማር፤ ድራማና ሙዚቃ
- ወጣት ለወጣት ውይይት
- የገቢ ምንጭ ማፈላለግና የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ
- የኮንዶም ሽያጭ ስለጠና መስጠት ናቸው ፡፡

በ3 ዓመታት ውስጥም 222 እናቶች ሪፈር ተደርገው የፊስቱላ ህክምና አግኝተዋል፡፡

የጤና ትምህርትና የመረጃ ስርፀት

በተዋልዶ ጤና ዘርፍ የተካተቱ የእናቶችና ህፃናት አገልግሎቶች የሚተገበሩበት አንዱ የአፈፃፀም ስልት የጤና ትምህርትና የመረጃ ስርፀት ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተለያዩ የተዋልዶ ጤና ዘርፎች የተከናወኑ የመረጃ፤ የትምህርትና የግንኙነት (IEC) ሥራዎች በሰንጠረዡ ላይ ተመልክተዋል፡፡

የተ/ጤ/ዘርፍ	ክንውን
የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት	11,278,255
የእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎት	11,351,153
የኤች አይ ቪ ኤድስ አገልግሎት	15,505,330
ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል	10,863,679

ለአልማ ፀረ-ፊስቱላ ክበቦች ሽልማት ሲሰጥ

በአልማ የተገነቡ የጤና ተቋሞች

ተቁ	የተገነባበት አመት	ዞን	ወረዳ
1	1988	ሰ/ጐንደር	በለሳ
2	1988	ሰ/ጐንደር	ጭልጋ
3	1996	ሰ/ጐንደር	ጭልጋ
4	1989	ሰ/ጐንደር	ደባርቅ
5	1990	ሰ/ጐንደር	ዳባት
6	1991	ሰ/ጐንደር	ደንቢያ
7	1996	ሰ/ጐንደር	መተማ
8	1996	ሰ/ጐንደር	መተማ
9	1991	ሰ/ጐንደር	ቋራ
10	1996	ሰ/ጐንደር	ቋራ
11	1996	ሰ/ጐንደር	ቋራ
12	1996	ሰ/ጐንደር	ቋራ
13	1995	ሰ/ጐንደር	ም/በለሳ
14	1989	ደ/ጐንደር	ፋርጣ
15	1995	ም/ጐጃም	ደጀን
16	1988	ም/ጐጃም	እንብሴ
17	1989	ም/ጐጃም	እነማይ
18	1990	ም/ጐጃም	እነማይ
19	1990	ም/ጐጃም	ጐዛምን
20	1995	ም/ጐጃም	ሁለት እጁ እነሴ
21	1989	ም/ጐጃም	ባህርዳር ዙሪያ
22	1988	ም/ጐጃም	ቡሬ
23	1995	ም/ጐጃም	ቡሬ
24	1990	ም/ጐጃም	ደጋዳሞት
25	1989	ም/ጐጃም	ጃቢ ጣህናን
26	1988	ሰ/ሸዋ	በረኸት
27	1990	ሰ/ሸዋ	በረኸት
28	1988	ሰ/ሸዋ	ሚዳ
29	1988	ሰ/ሸዋ	ምንጃር
30	1990	ሰ/ሸዋ	ሞረትና ጅሩ
31	1995	ሰ/ሸዋ	ሞገራ
32	1998	ሰ/ሸዋ	ቀወት
33	1998	ሰ/ሸዋ	ቀወት
34	1998	ሰ/ሸዋ	ቀወት
35	2000	ሰ/ሸዋ	ግሸን ራቤል
36	2000	ሰ/ሸዋ	ግሸን ራቤል
37	1989	ሰ/ወሎ	ቡግና
38	1989	ሰ/ወሎ	ግዳን
39	1991	ሰ/ወሎ	ጉባላፍቶ
40	1990	ሰ/ወሎ	ሃብሩ
41	1995	ሰ/ወሎ	ሃብሩ
42	1988	ሰ/ወሎ	ቆቦ
43	1991	ሰ/ወሎ	መቄት
44	1991	ሰ/ወሎ	መቄት
45	1989	ሰ/ወሎ	ዋድላ
46	2001	ሰ/ወሎ	ላስታ
47	2001	ሰ/ወሎ	ቡግና
48	1988	ደ/ወሎ	አቅስታ
49	1991	ደ/ወሎ	ኮምቦልቻ
50	1990	ደ/ወሎ	ኩታበር
51	1995	ደ/ወሎ	ተሁለደሬ
52	1990	ደ/ወሎ	ተንታ
53	1989	ደ/ወሎ	ወረባቦ
54	1987	ደ/ወሎ	ወግዲ
55	2000	ደ/ወሎ	ቃሉ
56	2000	ደ/ወሎ	ቃሉ
57	2000	ደ/ወሎ	ቃሉ
58	2000	ደ/ወሎ	ቃሉ
59	2000	ደ/ወሎ	ወረኢሉ
60	2000	ደ/ወሎ	ወረኢሉ
61	2000	ደ/ወሎ	ወረኢሉ
62	2000	ደ/ወሎ	ሲ.ጋንቦ
63	2000	ደ/ወሎ	ሲ.ጋንቦ
64	2000	ደ/ወሎ	ሲ.ጋንቦ
65	2001	ደ/ወሎ	ፎገራ
66	2001	ደ/ወሎ	ለገሂዳ
67	2001	ደ/ወሎ	ለገሂዳ
68	1990	ዋግ ኽምራ	ዳህና
69	1987	ዋግ ኽምራ	ዝቋላ
70	1988	ዋግ ኽምራ	ዝቋላ
71	1990	ኦሮሚያ	አርጡማ
72	1987	ኦሮሚያ	ባቲ
73	1988	ኦሮሚያ	ደዋጨፋ
74	1990	ኦሮሚያ	ከምከም
75	1989	ኦሮሚያ	ስማዳ
76	1995	ኦሮሚያ	ታች ጋይንት
77	1988	አዊ	አንከሻ
78	1990	አዊ	ባንጃ
79	1988	አዊ	ዳንግላ
	7አመት	10 ዞኖች	49 ወረዳዎች

የእንስሳት ጤና ኬላ ግንባታ

1	2001	ሰ/ወሎ	ወልድያ
2	2001	ሰ/ወሎ	ላስታ
3	2001	ሰ/ወሎ	ቡግና


‹‹ሁሉም ደንበኞቻችን በኑሮአቸው ላይ ትልቅ የመሻሻል
ለውጥ አሳይተዋል፡፡ ሴቶቹ አምራች ሆነዋል፡፡ በዚህም
ወንዶቹ ደስተኛ ናቸው፡፡ የገቢ መጠናቸው ከፍ እያለ ስለሆነ
ልጆታቸውን ያስተምራሉ፡፡
የእነሱ ልጆች በሚለብሱት ደህና
ልብሳቸው ያስታውቃሉ፡፡››
በላይነሽ ጉልቴ
የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪል
አልማ 1984-2002

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ አልማ 2002 ልማታዊ ሕብረትን ስፖንሰር ሲያደርግ ላቅ ያለ ደስታ ይሰማዋል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ለዘመናት ከምትታወቅበት በሽታ፣ ረሀብና ድህነት ሙሉ በሙሉ ተላቃ በሁለትና ሶስት አስርት አመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማድረስና ሀገራዊ ራዕያችን እውን እንዲሆን ለማስቻል ዜጎች ጤናማና አምራች የልማት ሀይል መሆን የግድ ይላል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የክልሉ መንግስት ለጤና የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት መሠረት በማድረግ መጭው ትውልድ ከበሽታ፣ ከረሀብና ከድህነት ነጻ እንዲወጣ እና ለተገልጋዮች ምቹና ቀልጣፋ የጤና አገልግሎት አሰራር ሥርዓት ከላይ እስከ ታች በሴክተሩ ለመዘርጋት የመሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ ጥናት አጥንቶ መተግበር በመቻሉ አመርቂ ውጤቶችን እያስመዘገበ ይገኛል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራማችን በመከላከል ላይ የተመሠረተውን የጤና ፖሊሲያችን ለመተግበር ዓይነተኛ መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን በቂ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በክልላችን ተንሰራፍተው የሚገኙትን ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም እናቶችና ህጻናትን ከሀይል ጥቃት፣ ከህመምና ሞት ለመታደግ አቅማችንን አሚጠን በመሥራት የምዕተ- ዓመቱን የልማት ግብ ለማሳካት በአመለካከትና በክህሎት ብቃት ያለው የልማት ሠራዊት በመፍጠር የዲሞክራሲ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጅምሮቻችንን በህዝቡ የነቃ-ተሳትፎ መምራት በመቻላችን አንጸባራቂ ድሎች ተመዝግበዋል፡፡

የተገኙ ምርጥ የጤና ተሞክሮዎቻችንን በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች በማስፋፋት የአርሶ አደሩን የማምረት አቅም ለማሳደግና የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ መከላከልን መሠረት ያደረገ የህዝብ ጤና ጥበቃ ሥራችንን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ይኖርብናል፡፡

በመሆኑም መላው የክልላችን ህዝብ፣ የአመራር አካላትና የጤና ዘርፍ ሠራተኞች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ አጋር ድርጅቶች ከምንጊዜውም በበለጠ ለጤና ሥራዎቻችን ከፍተኛ ትኩረት በመሥጠት ከጎናችን እንዲሠለፉ ጤና ጥበቃ ቢሮ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ለጤናችን በጋራ እንሥራ!

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ

ባህር ዳር / 2002 ዓ.ም.

የአልማ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች-የጤና ሃዋርያት

አልማ በጤናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ተግባሮች አንዱ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ነው፡፡ በአራማ ብሔራዊ ክልል በአሥሩም ዞኖች ወደሚገኙ 102 ወረዳዎች የተሰማሩ፣ በጤና ሐዋርያነት አግልግሎቱን ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ የሚያደርሱ 2,904 የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎችም አሉት፡፡ እነዚህ ወኪሎች በቅድሚያ አጠር ያለና ለተልዕኮአቸው የሚያበቃ የተዋልዶ ጤና ነክ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎችን ልዩ የሚያደርጋቸው ተወልደው ባደጉበት አካባቢና ሕብረተሰብ ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ መሆናቸው ነው፡፡ ይህም፣ በስልጠና ያገኙትን መለስተኛ እውቀት እንግዳ ካልሆኑበትና ኖረውበት ካዳበሩት ትልቅ ከባቢያዊ እውቀት ጋር በቀላሉ አዋህደው ተግባራዊ እንዲያደርጉት ያስችላቸዋል፡፡ ውጤታማም ያደርጋቸዋል፡፡

ወደ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ጣርማ በር ወረዳ፤ ሲና ቀበሌ ተጉዘንም ይህን ልናረጋግጥ ችለናል፡፡ በዚህ ‹ሲና› በተሰኘው የገጠር ቀበሌ ውስጥ 4 የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች የሚገኙ ሲሆን፣ አንዷም በላይነሽ ጉልቴ ትባላለች፡፡

በላይነሽ ጉልቴ ወኪል ከሆነችበት ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በቤተሰብ ምጣኔ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በማስወገድና በእናቶችና ሕፃናት ጤንነት ረገድ የተሰሩ ሥራዎች አመርቂ ውጤት እያስገኙ ስለመሆናቸው ያስረዳችን በሚከተለው ሁኔታ ነበር፡፡

1- የቤተሰብ ምጣኔ

‹‹በአካባቢያችን በላይ በላዩ ላይ መውለድ በመበርከቱ ምክንያት ልጆቻቸውን መመገብ፣ማልበስና ማስተማር የማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረስ የተለመደ ነበር፡፡ ይህ የሚሆነው ‹ልጅ ሲሳይ ነው፡፡ ልጅና እሸት አይጠገብም፡፡ ልጅ ሲበዛ ለአረምና ለሌላ ሥራ ያግዛል፣ ስናረጅ ይጦሩናል› በሚል አስተሳሰብ ነው፡፡

‹‹አልማ በሰጠን ስልጠና መሠረት፣ ይህን ለማስተካከል ቤት ለቤት እየዞርን በየግላቸው እናወያያቸዋለን፡፡ በቅርብ አግኝተን በቅድሚያ የምናነጋግረው ሴቷን ነው፡፡ መጀመሪያ ‹ለምን እንዳልወለድ ፈለጋችሁ? መታቀፊያ ጠየቅኋችሁ?›› እያሉ ይቃወሙናል፡፡ በእነሱና በልጆቻቸው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ስናነሳላቸውም ‹የምታስቡልን ከሆነ ለምን ለልጆቻችን እርዳታ አታመጡልንም› ይሉናል፡፡ ወንዱም ‹ለምን መጡ?› ብሎ ይጠይቃል፡፡ ባለቤቱ ስትነግረው ይጣላናል፡፡ ‹ሁለተኛ ብትመጡ ውሻ ነው የምለቅባችሁ› ይለናል፡፡

‹‹ለማሳመን እስከ አምስት ጊዜም እንመላለሳለን፡፡ አሳመንን ስንልም አንዷ ያልሆነ ነገር አውርታ ታበላሽብናለች፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ለአምስት ዓመት የሚያገለግለውን የእርግዝና መከላከያ (implant) ‹የወር አበባ ያበዛል› እያለች በሌሎች ባሳመንኳቸው ደንበኞች ላይ ጥርጣሬ የምትፈጥር ነበረች፡፡ ይህን መከላከያ ራሴም ተጠቅሜ ችግር እንደማያመጣ ላሳያቸውና ላሳምናቸውም ሞክሬአለሁ፡፡ ወሬውን የነዛቸው ሴት ግን መከላከያውን አስወጣችውና በመካከል አረገዘች፡፡ ይህን በክንድ የሚቀበር ኖርፕላንት የተጠቀመ መካን እንደሚሆንም ይወራ ነበር፡፡ በአጋጣሚ የዚች ሴት ማርገዝ ግን ወሬው ስህተት መሆኑ እንዲታወቅ በማድረግ አስተምሮልኛል፡፡

‹‹የዚህ ዓይነቱን ውጣ ውረድ እያለፍን ነው ብዙዎችን ልናሳምን የቻልነው፡፡ ብዙ ደንበኛ የማፈራው በራሴ አስተማሪነት ብቻ አይደለም፡፡ ደንበኞች ራሳቸው እያሳመኑ ሌላ ደንበኛ ያመጣሉ፡፡ እርስ በርሳቸውም ይማማራሉ፡፡

‹‹ደንበኞቻችን በእኛ ላይ ትልቅ እምነት አላቸው፡፡ ትልቁ ስነምግባራችን ምስጢር መጠበቅ ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚነታቸው እንዳይታወቅ የሚፈልጉ አሉ፡፡ እርስ በርሳቸው የሚወያዩ እንደመናራቸው፣ በአገልግሎቱ እየተጠቀሙ እያሉም አንዱ የሌላውን የማያውቁ እንዳሉም እንታዘባለን፡፡ ይህ መተፋፈርና ለመታወቅ አለመፈለግ ጎላ ብሎ የሚታየው የደጋ ነዋሪዎች አካባቢ ነው፡፡

በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ የተመደቡ የመንግስት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችም ከአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ጋር በትብብር ይሰራሉ፡፡ በላይነሽ ጉልቴ በምትሰራበት ሲና ቀበሌ ያገኘናቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችም እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹በላይነሽ በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚያስቸግሯት ካሉ ትነግረኛለች፡፡ ሄጄም ለማሳመን እጥራለሁ፡፡ ዲፖ እንድትጠቀም ያሳመነቻት ሴት ስትኖርም ትልክልኛለች፡፡ እኔ ለተጠቃሚዋ እሰጣትና ተመልሼ ሪፖርት አደርግላታለሁ፡፡ ስለእያንዳንዱ ደንበኛ መረጃ እንለዋወጣለን፡፡››

ሚሊና ጎበዜ፡-የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ
ሰሜን ሸዋ ዞን፤ ጣርማ በር ወረዳ፤ ሲና ቀበሌ

‹‹የአካባቢውን ልዩ ባሕልና የአኗኗር ዘይቤ ከእኛ የበለጠ የሚያውቁት የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ናቸው፡፡ በምን መንገድ ቀርበን እንዴት እንደምናሳምናቸው ይነግሩናል፡፡ ሥራችን ተደጋጋፊ ነው፡፡››

ደስታ ኃይለ ገብርኤል፡- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ
ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ጣርማ በር ወረዳ፣ ሲና ቀበሌ

2- ኤች.አይ.ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር

ከአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ተልዕኮዎች አንዱ ኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ነው። በላይነሽ ጉልቴም ስለበሽታው ምንነት ሰፋ ያለ ግንዛቤ መፍጠር መቻላቸውን ትናገራለች። ሙሉ ቃሉ የሚከተለው ነው።

‹‹ስለበሽታው ምንነት ጥሩ ግንዛቤ መፍጠር ችለናል። ያለንበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ግን ብዙ ውጣ ውረድ አልፈናል። መልካም ግንዛቤ ከያዙ በኋላም 'በድንጋጤ እሞታለሁ' እያሉ ለመመርመር የሚፈሩ ያጋጥሙን ነበር። አሁን ግን እያስተማርን ለውጥ መጥቷል። መመርመር የተለመደ ሆኗል።

‹‹ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸው ባስተማርናቸው መሠረት ወደ ጤና ጣቢያ እየሄዱ መድኃኒቱን እየወሰዱ ነው። ቫይረሱ ያልተገኘባቸው ከፍ ያለ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። በአንድ መወሰን በስፋት ይታያል። ኮንዶም መጠቀም አልፎ አልፎ አለ። ወጣቱ አካባቢ መታቀብ በመለመድ ላይ ነው።››

3- ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ

የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች ዓይነት ብዙ በሆኑት ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ አላቸው። በሥምሪታቸው ላይ ከፍ ያለ አፅንኦት ሠጥተው የሚሰሩት ግን በየካባቢያቸው ሰፍነው በሚታዩት ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ነው።

ከበላይነሽ ጉልቴ እንደተረዳነው፣ የአልማ ወኪል በሆነችበት ጣርማ በር ወረዳና ሲና ቀበሌ የኖሩት ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች የሴት ልጅ ግርዛት፣ ጠለፋ፣ እንጥል ማስቆረጥ፣ ያለዕድሜ ጋብቻና ግግ ማስወለቅ ናቸው።

ዛሬ እነዚህ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እንደገነኑ የኖሩበት ዘመን እየተሻረ ይመስላል። ‹‹ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል›› ባይባልም፣ ብርቱና ብዙ ድካም የጠየቀ የማስተማር ሥራ በመሰራቱ ምክንያት፣ከበርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተቀባይነትን እያጡ በመሄድ ላይ ናቸው። ተከታዩ የበላይነሽ ጉልቴ አስተያየትም ይህን ያረጋግጣል።

‹‹ጠለፋ ሙሉ በሙሉ ቀርቷል ለማለት ይቻላል። ያለዕድሜ ጋብቻን ለማስቀረት የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች በስፋት ከማስተማራችን በተጨማሪ. መምህራንም በየት/ቤቱ ለተማሪዎች ያስተምሯቸዋል። በህግም የተከለከለ ሆኗል። ልጆች 'ያለዕድሜያችንና ያለፍላጎታችን አናገባም' እያሉ ቤተሰቦቻቸውን የሚከሱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። የቀበሌ መስተዳደርም ይህን ጉዳይ ይከታተለዋል። ስለዚህም፣ ያለዕድሜ ጋብቻ እንደተወገደ መናገር እችላለሁ።

‹‹ግግ ማስወለቅ የሚከሰተው አልፎ አልፎና በድብቅ ነው፤ ብዙም የለም። እንጥል መቁረጥም ጎጅነቱ እየታወቀ ነው። ወደ ሃኪም ቤት የሚወስዱት እየበዙ መጥተዋል። በኤች አይ ቪ ኤድስ ላይ የፈጠርነው ጠንካራ ግንዛቤ ለእንጥል መቁረጥ መቀነስ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮልናል። ንፅህናው ባልተጠበቀ ስለት እንጥል መቁረጥ ለኤች አይ ቪ የሚዳረግ መሆኑን ስለምንነግራቸው በቀላሉ ተቀባይነት ያገኛል።

‹‹በዝቶ ያልቀነሰውና ሰፋ ብሎ የሚታየው ጎጅ ልማዳዊ ድርጊት የሴት ልጅ ግርዛት ነው። በእርግጥ፣ ወጣቱ ትውልድ ላይ ትልቅ ለውጥ አለ። የሴት ልጅ ግርዛት ጎጅ መሆኑን የማያምኑት ትላልቆቹ ሰዎች ናቸው።››

4- የእናቶችና የሕፃናት ጤንነት

የእናቶችና የሕፃናት ጤንነትን በመንከባከብ ረገድም የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪሎች መልካም ተግባር እያከናወኑ ነው። አሁንም ከበላይነሽ ጉልቴ ያገኘናቸውን ፍሬ ቃሎች በዋቢነት አቅርበናቸዋል።

‹‹ነፍሰ ጡር እናቶች የህክምና ክትትል እንዲያደርጉ እናስተምራለን፣ እንመክራለን። አዲስ ነፍሰ ጡሮች ይህን ለማድረግ ስለሚያፍሩና ስለሚፈሩ ራሳችን ወደ ሀኪም ይዘናቸው እንሄዳለን።

‹‹ከወሊድ በኋላም ህፃናቱን ከ45 ቀን እስከ 9 ወር ድረስ እንዲያስከትቡ እየነገርናቸውና እየተከታተልናቸው፣ ክትባቱን ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እንዲያገኙ እናደርጋለን።

‹‹በአጠቃላይ አልማ እናቶች ጤነኛ እንዲሆኑና፣ ሕፃናት በጤንነት ተወልደው በጤንነት እንዲያድጉ የሚያግዝ ትልቅ ሥራ እየሰራ ነው።››

አልማን ይደግፉ!

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ)
Amhara Development Association (ADA)

አድራሻ: ባህርዳር ስልክ: 058 220 0983 ፋክስ: 058 220 1088 ፖ.ሳ.ቁ. 307 e:mail ada.hq@ethionet.et
አዲስ አበባ ስልክ: 011 551 7886 ፋክስ: 011 551 7795 ፖ.ሳ.ቁ. 13685 e:mail ada.liaison@ethionet.et
www.amharada.org

ከአልማ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚዎች አንደበት

የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ 18 ሚሊዮን እንደሚሆን ይገመታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎትን የሚያገኙት የክልሉ ነዋሪዎች ደግሞ 9 ሚሊዮን ናቸው፡፡ እነዚህ 9 ሚሊዮን ወገኖች ከአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ያተረፉትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይናገሩ ዘንድ ቢጠየቁ፣ የብዛታቸውን ያህል የበዛ ድምፅ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ አንደበታቸው አንድ፣ ከአንደበታቸው የሚፈልቀው ልሳንም አንድ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ ሦስት የገጠር ቤተሰቦች ያገኘነው ቃልም የሁሉንም ይወክላል፡፡

ወይዘሮ እቴነሽ ተክለፃድቅ እና ወታደር ሠይፈ ገብረ ፅዮን

ከሰሜን ሸዋ ዞን፣ ጣርማ በር ወረዳ፣ ሲና ቀበሌ

አልማን መደገፍ ጤነኛና አምራች ዜጋ መፍጠር ነው

አልማን ይደግፉ!

አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ)
Amhara Development Association (ADA)

አድራሻ: በህርዳር ስልክ: 058 220 0983 ፋክስ: 058 220 1088 ፖ.ሳ.ቁ. 307 e:mail ada.hq@ethionet.et
አዲስ አበባ ስልክ: 011 551 7886 ፋክስ: 011 551 7795 ፖ.ሳ.ቁ. 13685 e:mail ada.liaison@ethionet.et
www.amharada.org

‹‹እኛ ለ18 ዓመት አንድ ላይ በትዳር ቆይተናል፡፡ ሦስት ልጆች አሉን፡፡ ሦስቱን ልጆቼን ስወልድ ለማራራቅ ብዬ በየጣልቃው ክኒን እወስድ ነበር፡፡ ከሦስት ልጅ በኋላ ግን መጨመር አልፈለግሁም፡፡ የዘለቄታ መከላከያውን ወሰድኩኝ፡፡ ያኔ የአራት ወር ልጅ አቅፌ ነበር፡፡

‹‹ይህን ላደርግ የቻልኩት የአልማ የተዋልዶ ጤና ወኪሎች አስተምረውኝ ነው፡፡ ሲያስተምሩኝ አላንገራገርኩም፡፡ ቶሎ ነው የተቀበልኳቸው፡፡



ወታደር ሠይፈ ገብረፅዮንም የባለቤታቸው የወይዘሮ እቴነሽን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡

‹‹የዘለቄታ የእርግዝና መከላከያውን እንድትወስድ ሁለታችንም ተወያይተናል፡፡ በውይይታችን ላይ የተፈጠረ አለመግባባት አልነበረም፡፡

‹‹አስቀድመንም አራርቀን መውለዳችን የሰጠን ግንዛቤ አለ፡፡ ትልቁ ትንሹን በኃላፊነት ሲያጫውተው፣ እኛ በሌለንበት ተንከባክቦ ሲያቆየው አይተናል፡፡››

ወይዘሮ እቴነሽ የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለጤናም ሆነ ለሥራ የሚበጅ መሆኑን ሲናገሩም፡-

‹‹እኔ ጤነኛ ነኝ፡፡ ጤነኛ በመሆኔ የማሳ ሥራም እሰራለሁ፡፡ አሁን እዚህ መጥታችሁ ስታናግሩኝ እንኳ የባቄላ ማሳችንን እያረምኩ እንደነበር ተመልክታችኋል፡፡ አራርቄና መጥኜ ባልወልድ ህመምተኛ ሆኜ የአልጋ ቁራኛ እሆን ነበር፡፡ በሕይወት አለመኖርንም ያስከትላል፡፡

‹‹እንኳን የማሳውን የቤቱንም ሥራ መስራት የሚቻለው ጤና ሲኖር ብቻ ነው፡፡ በአካባቢያችን የሚኖሩ የብዙ ሴቶችን ሁኔታ እታዘባለሁ፡፡ አንድ አዝላ፣ አንድ አቅፋ፣ ሌላውን ፀንሳ የቤት ውስጥ ሥራ ልትሠራ የሚያስቸግራትም አለች›› ይላሉ፡፡

አራርቀውና መጥነው የወለዷቸው ልጆቻቸውስ ምን ይመስላሉ? ለዚህ መልስ የሰጡን አባታቸአው ወታደር ሰይፈ ገብረ ፅዮን ናቸው፡፡

‹‹ልጆቻችን የጫጬ አይደሉም፡፡ የፋፉ ናቸው፡፡ በአስተዳደግም በጥሩ ሁኔታ እያሳደግናቸው ነው፡፡ በአመጋገባቸው፣ በልብሳቸው፣ በጤናቸው ደህና ናቸው፡፡ እያስተማርናቸውም ነው፡፡››

ወይዘሮ እቴነሽና ወታደር ሠይፈ ራሳቸውን የአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት መልዕክተኛ አድርገው ይቆጥራሉም፡፡ በየአጋጣሚው ሌሎችም የአግልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማስተማር ወደ ኋላ አይሉም፡፡

‹‹እኔ ለጓደኞቼም እነግራለሁ፡፡ ለምሳሌ አንድ ጓደኛዬ አለች፡፡ 8 ወልዳለች፡፡ ‹ከዚህ በኋላ በቃሽ፣ የዘለቄታውን ባትጠቀሚም የጊዜያዊውን መውሰድ ትችያለሽ› እያልኩ እመክራታለሁ፡፡ ‹እሺ› ብላኛለች፡፡ ብሶት በዝቶባታል፡፡ እየወሰነች ይመስለኛል፡፡››

ይህን ያሉን ወይዘሮ እቴነሽ ሲሆኑ፣በተመሳሳይ ሁኔታ ወታደር ሰይፈም የሚሉት አላቸው፡፡

‹‹በእኔ በኩልም በግልም ሆነ በስብሰባ ላይ እነሳለሁ፡፡ ‹የእኛንና የእናንተን ኑሮ ተመልከቱ› እያልን ያገኘነውን ጥቅም እንነግራቸዋለን፡፡ ብዙ ሰዎች እየሰሙን ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ተገልጋዮች እየበዙ በመሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ አልማን በጣም ነው የምናመሰግነው፡፡››

‹እኔ ጤነኛ ነኝ፡፡ ጤነኛ በመሆኔ
የማሳ ሥራም እሰራለሁ፡፡ አሁን
እዚህ መጥታችሁ ስታናግሩኝ እንኳ
የባቄላ ማሳችንን እያረምኩ
እንደነበር ተመልክታችኋል፡፡

‹‹ልጆቻችን የጫጩ አይደሉም፡፡
የፋፉ ናቸው፡፡ በአስተዳደግም
በጥሩ ሁኔታ እያሳደግናቸው ነው፡፡
በአመጋገባቸው፣ በልብሳቸው፣
በጤናቸው ደህና ናቸው፡፡
እያስተማርናቸውም ነው፡፡››

ወይዘሮ ፀዳለ ሰይፉ እና አቶ መኮንን ታዬ
ከሰሜን ሸዋ ዞን፣ አንጎለላና ጠራ ወረዳ፣ ኮቱ ቀበሌ

ወይዘሮ ፀዳለ ሰይፉ እና አቶ መኮንን ታዬ
ከአልማ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ወኪል ከወይዘሮ አልማዝ ማሞ ጋር

‹‹ሁለት ልጆች አሉን፡፡ ትንሽ ልጃችን 13 ዓመቷ ነው፡፡ እሷ ክርስትና ከተነሳች ጀምሮ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚ ነኝ፡፡ የመጀመሪያዋን በወለድኩ በሁለተኛው ዓመት ነው የወለድኳት፡፡ ሁለትም ቢሆን አከታትሎ መውለድ ይጎዳል፡፡ ኑሮዬ

የተጎሳቆለ ነበር፡፡ ያኔ ሥራ መሥራት አልችልም፡፡ የመንታ እናት ያህል ነኝ፡፡ ሁለቱም ያለቅሳሉ፡፡ ማባበል አለብኝ፡፡ አንዷን አቅፌ፣ አንዷን አዝየ አባብላለሁ፡፡ እንደዚያ ሆኖ በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጪ ሥራ መሥራት አይቻልም፡፡

‹‹መጀመሪያ ሃኪም ቤት ሄድኩና ሃኪሞች ስለ ቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት ሰጡኝ፡፡ ለመቀበል አልተቸገርኩም፡፡ ወዲያውኑ ወስጄ ክኒኑን እጠቀም ነበር፡፡ አሁን ግን መርፌውን ነው የምወስደው፡፡ በእርግጥ፣ መጀመሪያ ብዙም አልደፈርኩትም ነበር፡፡ የበለጠ የገፋፋኝ ባለቤቴ ነው፡

‹‹መውለዱን ከተውኩ ጀምሮ ጤነኛ ነኝ፡፡ ትኩሳትም አሞኝ አያውቅም፡፡ በአካልም ጠንካራ ነኝ፡፡ ጤነኛና ጠንካራ በመሆኔ በቤት ውስጥ ያለውን ሥራ ያለችግር አከናውናለሁ፡፡ ከብቶቻችንንም እንከባከባለሁ፡፡ በራሴ በኩል አምራች ነኝ፡፡

‹‹እኔ መልዕክቱን ለብዙዎች አስተላልፋለሁ፡፡ ‘የወሊድ መከላከያ የማህፀን በሽተኛ ያደርጋል› የሚሉ ያጋጥሙኛል፡፡ ጠቃሚነቱን አውቀው የሚቀበሉና እኔ ነግሬአቸው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑም አሉ፡፡

‹‹የአልማ የተዋልዶ ጤና አግልገሎት ወኪሎች ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ጭምር ያስተምሩናል፡፡ አንድ ለአንድ እንድንወሰን እየነገሩን ስለመተላፊያ መንገዶቹና ስለጥንቃቄውም ያስተምሩናል፡፡ ተግባራዊ እደረግነው ነው፡፡

‹‹በጎጅ ልማድ በኩልም እንጥል ማስቆረጥና የሴት ልጅ ግርዛት ጎጅ መሆኑን ይነግሩናል፡፡ በእኛ በኩል የልጆቻችንን እንጥል አስቆርጠን አናውቅም፡፡ ሁለቱም ልጆቻችን አልተገረዙም፡፡

‹‹አልማ እስከዛሬም አገልግሎቱን ይሰጠናል፡፡ ወኪሎቹ ከጎናችን ተለይተው አያውቁም፡፡ ለወደፊትም ባይለዩን ጥሩ ነው፡፡››

ወይዘሮ ፀዳለ ሰይፋ




‹‹መውለዱን ከተውኩ ጀምሮ ጤነኛ ነኝ፡፡ ትኩሳትም
አሞኝ አያውቅም፡፡ በአካልም ጠንካራ ነኝ፡፡ ጤነኛና
ጠንካራ በመሆኔ በቤት ውስጥ ያለውን ሥራ ያለችግር
አከናውናለሁ፡፡ ከብቶቻችንንም እንከባከባለሁ፡፡ በራሴ
በኩል አምራች ነኝ፡፡

‹‹ልጆታችን አይራቡብንም፡፡
አይራቆቱብንም፡፡ በምግባቸውም ሆነ
በልብሳቸው አቅማችን በሚፈቅደው
መጠን እንንከባከባቸዋለን፡፡